መልእክት አሥር

**የጌታ ምለሳ—ጽዮንን መገንባት**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፡- መዝ. 48፡2፤ 11-12፤ 20፡2፤ 50፡2፤ 53፡6፤ 87፡2፤
ራእ. 2፡7፣ 11፣ 17፣ 26-28፤ 3፡5፣ 12፣ 20-21

**I. ጽዮን የንጉሥ ዳዊት ከተማ (2 ሳሙ. 5፡7)፣ ቤተ መቅደሱ በምድር ላይ እንዳለ የእግዚአብሔር መኖሪያ ስፍራ የተገነባባት የኢየሩሳሌም ከተማ ማዕከል ነበረች (መዝ. 9፡11፤ 2፡6፤ 74፡2፤ 76፡2፤ 125፡1፤ 135፡21፤ ኢሳ. 8፡18)፡-**

ሀ. ኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያንን በምሳሌ ታሳያለች፣ ጽዮን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉትን ድል ነሺዎች በምሳሌ ታሳያለች፡-

1. ጽዮን የኢየሩሳሌም ድምቀት፣ የቅድስቲቱ ከተማ ውበት ናት—መዝ. 48፡2፤ 50፡2።
2. እንደ የቅድስቲቱ ከተማ ኢየሩሳሌም ድምቀት እና ውበት፣ ጽዮን ድል ነሺዎቹን እንደ የቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ጫፍ፣ ማዕከል፣ ከፍ መደረግ፣ መጠንከር፣ መበልጠግ፣ ውበት እና እውነታ በምሳሌ ታሳያለች—48፡2፣ 11-12፤ 20፡2፤ 53፡6፤ 87፡2።
3. የጽዮን ተራራ ለጌታ ሙሉ በሙሉ ክፍት እና በእርሱ ሙሉ በሙሉ የተያዘች ናት—24፡1፣ 3፣ 7-10።

ለ. ድል ነሺዎቹ እንደ ጽዮን የክርስቶስ አካል እውነታ ናቸው፣ [በወደፊት] ዘላለም የምትጠናቀቀውን ቅድስት ከተማ፣ አዲሲቱን ኢየሩሳሌም፣ እንደ የእግዚአብሔር መኖሪያ ከፍተኛ-የመጨረሻ-ምርጥ ቅድስተ ቅዱሳን ለማምጣት በአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት የክርስቶስን አካል መገንባት ያጠናቅቃሉ—ራእ. 21፡16፣ ተዛ. ዘጸ. 26፡2-8፤ 1 ነገ. 6፡20።

ሐ. ቤተ ክርስቲያን የዛሬዋ ኢየሩሳሌም ናት፣ በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥም እንደ የዛሬው ጽዮን የድል ነሺዎች ቡድን መኖር አለበት—ሮሜ 12፡4-5፤ ኤፌ. 4፡16፤ ራእ. 2፡7፤ 3፡12፡-

1. አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት የእግዚአብሔር ግብ እንዳልሆኑ፣ ነገር ግን እግዚአብሔር ግቡ ላይ ለመድረስ የሚወስደው የክንውን ሂደት እንደሆኑ ይህ ይገልጣል፤ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ወደ የክርስቶስ አካል እውነታ ውስጥ ያስገቡናል።
2. የእግዚአብሔርን ኢኮኖሚ ማከናወን የሚችለው የጌታ ምለሳ ከፍተኛው ጫፍ እግዚአብሔር ብዙ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትን በውጫዊ መልኩ ማፍራት ሳይሆን የእርሱ ሕያው አካሉ እንዲሆን ሕይወታዊ አካል ማፍራት ነው—1 ቆሮ. 12፡27፤ ኤፌ. 4፡16።

**II. የጌታ ምለሳ ምን እንደሆነ ልንገነዘብ ይገባል፤ የጌታ ምለሳ ጽዮንን ለመገንባት ነው—ራእ. 14፡1፤ ኤፌ. 4፡16፤ ራእ. 21፡2፣ 9-10፡-**

ሀ. የኢየሩሳሌም መለያ ባሕሪ፣ ሕይወት፣ በረከት እና ምሥረታ የሚመጡት ከጽዮን ነው—1 ነገ. 8፡1፤ መዝ. 51፡18፤ 102፡21፤ 128፡5፤ 135፡21፤ ኢሳ. 41፡27፤ ኢዮኤል 3፡17።

ለ. በራእይ መጽሐፍ ጌታ የሚፈልገው እና ጌታ የሚገነባው ጽዮንን፣ ድል ነሺዎችን ነው፤ በቅዱሱ የእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ያለው የመንፈሳዊው መገለጥ ውስጠ-መሠረታዊ እውነታ ይህ ነው፤ እኛ ማንኛውም አይነትን ዋጋ በመክፈል ለመጸለይ እና ሐዋርያው ጳውሎስ እንደከፈለው ዋጋ ለመክፈል በእርግጥ ሌላ ተስፋ እስከማይኖረን ድረስ መፈለግ አለብን።

ሐ. ለጌታ የድል ነሺዎች ጥሪ በዚህ ዘመን ውስጥ ያለው ምላሻችን ሕያው-ንቁ መሆናችን ነው፤ ሕያው-ንቁ መሆን ማለት ሕያው እና ንቁ ከሆነው አምላካችን ጋር በአንድነት ሕያውና ንቁ መሆን ነው፤ ለዘላለማዊ ኢኮኖሚው መፈጸም በምድር ላይ ያለው የእግዚአብሔር እንቅስቃሴ ከፍተኛ-መጨረሻ-ምርጥ በሆነ መልኩ በድል ነሺዎቹ አማካኝነት ነው—ዳን. 11፡32፤ ዕብ. 3፡12፤ 9፡14፤ ተዛ. ራእ. 3፡1።

መ. በጽዮን የተመሰሉት ድል ነሺዎች፣ እንደ የክብር ንጉሥ ጌታ መላው ምድርን እንደ መንግሥቱ ለመውረስ ተመልሶ የሚመጣባቸው ግንባር ናቸው—መዝ. 24፡1፣ 3፣ 7-10፤ ዳን. 2፡34-35፤ 7፡13-14፤ ኢዮኤል 3፡11፤ ራእ. 11፡15፤ 19፡13-14።

ሠ. ከመጸለይ ውጭ ወደ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ ከፍተኛ ጫፍ፣ የክርስቶስ አካል እውነታ የምንደርስበት ሌላ መንገድ የለም፤ የክርስቶስ ሙሽራ እንሆን ዘንድ እንደ የክርስቶስ አካል እውነታ ድል ነሺዎች መሆናችን ይህን ዘመን፣ የቤተ ክርስቲያንን ዘመን ይዘጋል፣ በመንግሥቱም ዘመን ይህችን ምድር ይወስድ፣ ይይዝ እና ይገዛ ዘንድ ክርስቶስን እንደ የክብር ንጉሥ ከድል ነሺዎቹ ጋር መልሶ ያመጣዋል—ቁ. 7-9፤ 20፡4፣ 6፤ መዝ. 24፡7-10።

ረ. ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎች የጻፈው መልእክት በተዋሐደው መንፈስ በመኖር በክርስቶስ አካል እውነታ ውስጥ የሚኖሩትን ድል ነሺዎች ኑሮ ይገልጣል፡-

1. የክርስቶስ አካል እውነታ በእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ውስጥ ከፍተኛው ጫፍ እና በጥበብ እና የመገለጥ መንፈስ አማካኝነት የተገለጠ የመጽሐፍ ቅዱስ ከፍተኛው መገለጥም ነው—1፡17፣ 22-23።
2. የእግዚአብሔር የመኖሪያ ስፍራ፣ የእግዚአብሔር ቤት፣ የዛሬዋ ቤቴል፣ የሰማያት ደጅ እና ቅድስተ ቅዱሳን፣ በታቦቱ እንደ ምሳሌ የታየው እንደ የሦስታንዱ አምላክ አካል መልበስ የእስትንፋሳዊው ክርስቶስ መኖሪያ ስፍራ የሆነው የክርስቶስ አካል እውነታ በተዋሐደው መንፈስ የሆነ ኑሮ ነው—ቁ. 17፤ 2፡22፤ 3፡5፣ 16፤ 4፡23፤ 5፡18፤ 6፡18፤ ዘፍ. 28፡12-17፤ ዮሐ. 1፡51፤ ዕብ. 9፡3-4፤ 10፡19-22።
3. የክርስቶስ አካል እውነታ፣ በአራቱ ወንጌላት እንደተዘገበው የኢየሱስ ሕይወት እውነተኛው ሁኔታ፣ በኢየሱስ ያለ እውነታ፣ ዳግም ከተወለደው መንፈሳቸው ጋር በተዋሐደው በሚያድሰው መንፈስ አእምሮአቸው በመታደሱ አማካኝነት ፍጹም በተደረጉ አምላክ-ሰዎች እንደ የጋራ ኑሮ በብዙ ብልቶቹ ውስጥ መባዛቱ ነው—ኤፌ. 4፡1-6፣ 15-16፣ 20-24፤ ገላ. 2፡20፤ ፊልጵ. 1፡19-21፤ 4፡11-13።
4. የክርስቶስ ቅዱስ፣ ውብ፣ እግዚአብሔርን የምትገልጥ ሙሽራ፣ ነቀፋና የሌለባት ወይም ፍጹምነት ያልጎደላት እንሆን ዘንድ ቤተ ክርስቲያን ከመንፈሳችን ጋር በተዋሐደው በሚያስውበው፣ ሙሽራ በሚያዘጋጀው መንፈስ ተሞልታለች—ኤፌ. 5፡18፣ 26-27፤ ኢሳ. 60፡7፣ 19፤ 62፡3፤ ዘጸ. 28፡2፤ ተዛ. መዝ. 27፡4፤ 48፡2፤ 50፡2፤ 110፡2-3፣7፤ ኢሳ. 28፡5፤ 60፡21፤ 61፡3።
5. በመላው ማንነታችን ላይ ክርስቶስ ድል ነሺ ይሆን ዘንድ፣ በመንፈስ መለኮታዊ ሕይወት ሰይጣንን፣ ኃጢአትን እና ሞትን መግዛት እንድንችልና ጤነኛ የአካሉን ሕይወት፣ ጤነኛ የቤተ ክርስቲያን ሕይወት እንድንኖር እኛን በማስቻል፣ የእግዚአብሔር ጠላት የሆነ ነገር ሁሉ በውስጣችን ይገደል ዘንድ ከመንፈሳችን ጋር የተዋሐደውን የሚገድለውን መንፈስ መለማመድ አለብን—ኤፌ. 6፡10-18፤ መዝ. 48፡12-13።

## III. ድል ነሺዎቹ ክርስቶስን *ሥጋ* እንደለበሰው ሦስታንዱ አምላክ፣ እንደ አምላክ-ሰው ይደሰታሉ—"አንተን ብርታታቸው ያደረጉ፣ በልባቸው የጽዮንን መንገድ የሚያስቡ ቡሩካን ናቸው። በልቅሶ ሸለቆ በሚያልፉበት ጊዜ፣ የምንጭ መፍለቂያ ቦታ ያደርጉታል፤ የበልጉም ዝናብ ያረሰርሰዋል። ከኀይል ወደ ኀይል ይሸጋገራሉ፤ እያንዳንዱም በጽዮን ባለው አምላክ ፊት ይቀርባል"—84፡5-7 (አ.መ.ት.)፡-

ሀ. መገፈፎቹ እና ልቅሶዎቹ የእግዚአብሔርን ቤት ውበት እና ጣፋጭነት ያመጣሉ—ቁ. 1፣ 6 እና የግርጌ ማስታወሻ 1[1] እና 6[1]፤ ተዛ. 73፡26 እና የግርጌ ማስታወሻ 1።

ለ. ስናለቅስ ሳለን በመንፈስ እየተሞላን ነው፣ መንፈስም ለእኛ ምንጭ እና የቀደመው ዝናብ ይሆንልናል፤ ወደ ጽዮን የሚወስዱት መንገዶች ሁለት ዓምዶች እንዳሏት የእግዚአብሔር ቤት ወደ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የመግባት ውጥናችንን ያመለክታሉ፣ እነዚህም *ሥጋ* የለበሰውን የሦስታንዱን አምላክ *ሥራ* ቀዳሚ መጠናቀቆች፣ ለክርስቶስ መጨመር እንደ የእግዚአብሔር አካል መልበስ ክርስቶስን ያመለክታሉ—84፡3-6።

ሐ. በእግዚአብሔር መኖሪያ ቤት የመኖራችን በረከቶች፣ እንደ ጸሐይ በሕይወት አቅርቦት እኛን ለመሙላት (ዮሐ. 1፡4፤ 8፡12)፣ ከእግዚአብሔር ጠላቶች እንደ ጋሻችን እኛን ለመጠበቅ (ኤፌ. 6፡11-17)፣ እንደ ጸጋ ለድሰታችን (ዮሐ. 1፡14፣ 17) እና እንደ ክብር ለእግዚአብሔር በግርማ መገለጥ (ራእ 21፡11፣ 23) *ሥጋ* የለበሰውና የተጠናቀቀው ሦስታንዱ አምላክ ድሰታችን እንደሆኑ መዝሙር 84፡11 ይገልጣል።

## IV. *"መሠረቶቹ በተቀደሱ ተራሮች ናቸው፤ ....እግዚአብሔር የጽዮንን ደጆች ይወድዳቸዋል"—መዝ. 87፡1-2፡-*

ሀ. በቤተ ክርስቲያን ያሉት ድል ነሺዎች ምሳሌ የሆነችው ጽዮን፣ መሠረታቸው ክርስቶስ የሆኑት አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትን እንደ ምሳሌ በሚያሳዩት "በተቀደሱ ተራራዎች" ከፍተኛ ጫፍ ላይ ተገንብታለች (ቁ. 1)፤ የከበሩ ነገሮች የተነገሩላት ሰማያዊዋ ጽዮን (ቁ. 3) ለድል ነሺዎቹ የመጨረሻዋ የዕረፍት ቦታ ትሆናለች (ራእ. 14፡1)።

ለ. የጽዮን ደጆች ኅብረትን በማመልከት ለመግባት እና ለመውጣት ናቸው፤ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ለወደፊቱ አሥራ ሁለት በሮች ያላት የመሆኗ ሃቅ (21፡12፣ 21) የእግዚአብሔር ቅድስት ከተማ በኅብረት የተሞላች እንደምትሆን ያመለክታል።

ሐ. በእርግጥም ስለ ጽዮን፣ "ይህም ያም ሰው በእርሷ ውስጥ ተወለዱ፤/ ልዑልም ራሱ ያጸናታል" ይባላል። እግዚአብሔር ሕዝቡን ሲመዘግብ፣ "ይህ ሰው የተወለደው በዚያ ነው" ብሎ ይጽፋል (መዝ. 87፡5-6)፤ የቅዱሳን ሁሉ ጥቅል ድምር የሆነው፣ ("ይህ" እና "ያም") የሆነው ልዩና ብቸኛው፣ ክርስቶስ፣ ሁሉን ቅዱሳን እና በሁሉ ቅዱሳን የሆነው እርሱ ነው (ቆላ. 3፡11)።

መ. “ምንጩ ሁሉ በአንቺ ውስጥ ይገኛል” (መዝ. 87፡7 አ.መ.ት.)፤ ግብጽ በናይል ትመካ፣ ባቢሎንም በኤፍራጥስ ትመካ፤ ምንጮች የላቸውም፣ እኛ በጽዮን ያለን ግን አሉን።

**V. የመዓርግ መዝሙሮች (መዝ. 120—134) በቅዱሳን ልምምዶች እና ውዳሴዎች ውስጥ ስለ ጽዮን እና ስለ ኢየሩሳሌም ውድነት ያወራሉ፡-**

ሀ. መዝሙር 132 ወደ ጽዮን ከፍታ ከሚወጡበት ጉዟቸው ጋር በተገናኘ ሰባት ውድ ነገሮችን ይጠቅሳል፤ እነዚህ ነገሮች የቤተ ክርስቲያን ከፍታ ናቸው፣ በጽዮን በእግዚአብሔር ከፍተኛ ጫፍ ስላሉት ድል ነሺዎች ሁኔታ በስዕል ይናገራል—ቁ. 13-18፡-

1. ከእግዚአብሔር ጋር ማረፋቸው—“ይህች ለዘላለም ማረፊያዬ ናት”—ቁ. 14።
2. ከእግዚአብሔር ጋር መኖራቸው—“መርጫታለሁና በዚህች አድራለሁ”—ቁ. 14።
3. ለእርካታ ምግብ—“እጅግ አትረፍርፌ እባርካታለሁ፥ ድኾቿንም እንጀራ አጠግባለሁ”—ቁ. 15 (አ.መ.ት.)።
4. የከበረ ልብስ—“ካህናቶችዋንም ደኅንነትን አለብሳቸዋለሁ፥ ቅዱሳኖችዋም እጅግ ደስ ይላቸዋል”—ቁ. 16፤ ተዛ. ዘጸ. 28፡2።
5. የድል ቀንድ—“በዚያ ለዳዊት ቀንድን አበቅላለሁ”—መዝ. 132፡17።
6. የሚያበራ መብራት—“ለቀባሁትም ሰው መብራትን አዘጋጃለሁ”—ቁ. 17።
7. የሚያበራ ዘውድ—“ጠላቶቹን ኀፍረት አከናንባቸዋለሁ/ እርሱ ግን በላዩ ላይ የደፋው ዘውድ ያበራል”—ቁ. 18 (አ.መ.ት.)፤ ኢሳ. 62፡3።

ለ. በመዝሙር 132 እንደተሳለችው ጽዮን ስትገነባ የምንሰበሰብበት እና አብረን በአንድነት የምንኖርበት ስፍራ ይኖረናል፤ ይህ እንዴት መልካም እና ያማረ ነው!—መዝ. 133፡1-3።

ሐ. “ሰማይንና ምድርን የሠራ እግዚአብሔር ከጽዮን ይባርክህ” (134፡3)፤ አንዳንድ ድል ነሺዎች ባሉበት ስፍራ ሁሉ የእግዚአብሔር በረከት ይኖራል፤ ከጽዮን፣ ከከፍተኛው ጫፍ፣ ወደ ከፍተኛው ስፍራ ወደ ድል ነሺዎች ስፍራ ከደረሱ ሰዎች እግዚአብሔር ሁሌም ሕዝቡን ይባርካል፤ ከዚህ ስፍራ እግዚአብሔር ሕዝቡን ሁሉ ይባርካል።

**VI. ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ዘመን፣ ፍጹም የተደረጉት እና የበሰሉት አምላክ ሰዎች ጽዮን፣ ድል ነሺዎቹ፣ በአብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ያሉት ሕያው-ንቁ ቡድኖች ናቸው፣ ነገር ግን በአዲሱ ሰማይና ምድር፣ ከሁሉ አማኞች ጋር እንደ ድል ነሺዎች (ራእ. 21፡7 እና የግርጌ ማስታወሻ 1) መላዋ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ጽዮን ትሆናለች (ራእ. 21፡16)።**

© 2022 Living Stream Ministry